በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
ዋልድባን ለመታደግ የሚንቀሳቀስ ዓለም አቀፍ ጊዜያዊ
ኮሚቴ ዋሽንግተን ዲሲ

**Ethiopian Orthodox Tewahedo Church**
**Save Waldba Monastery International**
**Coalition Washington, DC**

ሐምሌ ፴ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# ታላቅ መንፈሳዊ ጉባኤ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን።

“. . . በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ . . .” ሉቃስ ፲፫ ፥ ፳፬

በዋሺንግተን ዲሲና አካባቢው ለምትኖሩ ኦርቶዶክሳዊያን በሙሉ፥

ጉዳዩ: በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አብያተ ክርስቲያናት እና ገዳማት ላይ እየተከሰተ ያለውን ጥቃት በተመለከተ ለመነጋገር እና ለመወያየት፤

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ታሪክ ማኅበራዊና ሥነ- ጥበብ እድገት ያበረከተችው አስተዋጽዖ ከኢትዮጵያ አልፎ በመላው ዓለም የሚታወቅ እውነታ ነው ። ቤተ ክርስቲያናችን ባላት ታሪክና መንፈሳዊ ሀብት ለበርካታ ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ትልቁን ድርሻ የምትይዝ ሲሆን በዚህም መንግሥትንና የተለያዩ ተቋማትን ተጠቃሚ እያደረገች ስትገኝ ፤ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ ቱሪስቶችም በዋነኛነት የቤተ ክርስቲያናችንን ጥንታዊያን ገዳማት አድባራት እና እንደ ጥምቀት መስቀል/ደመራ/ እና ልደት የመሳሰሉ ታላላቅ በዓላት መንፈሳዊ አከባበርን ለመመልከት እንደመጡ ዘወትር የሚመሰክሩት ነው ። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ ጥበብ እድገት ያበረከተችውን አስተዋጽዖ በየትኛውም ዘመን የነበረ እና ወደፊትም የሚኖር እንደሆነ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚመሰክረው እውነታ ነው።

እንደሚታወቀው ቅድስት ቤተክርስቲያን በበርካታ ችግሮች ከውስጥና ከውጪ እየተፈተነች ትገኛለች፥ በችግሮቹ ዙሪያ ለመወያየት እና ዘላቂ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለመፈለግ እና ለመወያየት በዋሽንግተን ዲሲ ሰዓት አቆጣጠር ከ4:00 PM. ጀምሮ በሚከተለው አድራሻ ተገናኝተን እንድንወያይ በቅድስት ቤተክርስቲያን ስም ጥሪያችንን እያቀረብን፥ የቅድስት ቤተክርስቲያንን ችግር ተነጋግሮ መፍትሄ መሻት የሁላችንንም ተሳትፎ ይጠይቃልና። እርስዎም የበሉልዎን አስተዋጽዖ እንዲያበረክቱ በድጋሚ በእግዚአብሔር ስም እንጠይቃለን። በዚህ ጉባኤ ላይ ሊቃውንት ቤተክርስቲያን፣ መምህራን፣ ዘማሪያን እንዲሁም ምሁራን ተጋብዘዋል፥ ኑና የበኩልዎን ያበርክቱ።

| አድራሻ: | የበለጠ መረጃ ቢያስፈልግዎ | ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|
| St. George Church Ballroom<br>4335 16th Street NW.<br>Washington, DC 20011 | 571-224-2869 ወይም 571-299-0975<br>savewaldba@gmail.com<br>PO Box 56145<br>Washington, DC 20040 | ነሐሴ ፮ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.<br>August 12, 2012<br>4:00 PM. (EST) |